# የእርሻ መሬት የይዞታ መብት ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ ችግሮች ላይ የተሰራ ጥናት

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች**፡-

ገብረመስቀል ገብረዋህድ

ሀና ብርሃኑ

ሕሊና መኮንን

ሰዊት ዘውዱ

በየክልሉ ያሉ የመሬትን ጉዳይ የሚያዩ ባለሞያዎች እነዚህም የመሬት አስተዳደር ኮሜቴዎች፣ የቀበሌ

የመሬት ዳኞችና አመራሮች የእውቀትና የተነሳሽነት ችግር ያለ መሆኑ በጥናቱ ግኝት ተመላክቷል። በመሆኑ በተለይም ከመሬት ዳኝነት ጋር በተያያዘ የህግ ዕውቀት የሚጠይቅ በመሆኑ፤ እነዚህ ሰዎች የሚሰጡት ውሳኔ በጥናቱ ከተደረገው ቃለመጠይቅ ውጤታማነቱና ፍታሐዊነቱ ላይ አጠያያቂ መሆኑ ተገልጿል። በመሆኑም በመሬት ዳኝነትና ከዘርፉ ጋር በተያየዘ የሚሰሩ ባለሞያዎች ከሚሰሩት ስራ ጋር በቂ እውቀት ያላቸውን በተመጣጣኝ ክፍይ መቀጠር ቢቻል በመጠኑም ቢሆን ችግሩን መቀረፍ ይቻላል።

የመሬትን ለመስጠት የሚቀመጡ መሰፈረቶችን ፍተዊነትና አተገባበር ላይ ችግር እንዳለ በጥናቱ ግኝት ላይ ተመላክቷል። በሕግ የተቀመጠውን በመተግበር ረገድም ሆነ ከገጠር መሬት ጋር ተያይዞ የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመቅረፍ ያለው የአሰራር ስርዐትን በተመለከተ ረጅም ጊዜ የሚወስድና የአርሶ አደሩን አቅም የሚፈትን በመሆኑ አሰራሩን ግልፅና ተጠያቂነት ያለበት፣አጭርና ቀልጣፋ በማድረግ ሂደቱን ማሳጠር የተሻለ ነው።ይህም ከገጠር መሬት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን፤ ጉዳዩ በተነሳበት ቦታ በአጭር ጊዜ ለመፍታትና ህበረተሰቡም መንግስት ላይ አመኔታ እንዲኖረው ያደረጋል። ይሕም አርሶ አደሩ ያለውን አቅም፣ ጉልበትና ጊዜ በልማት ላይ ብቻ እንዲያውል ይረዳል።

ከገጠር መሬት ጋር ተያይዞ ያለ መረጃን በተደረጃ ሁኔታ የማስቀመጥና የመሬቱ ባለቤት ለሆነው አካል መረጃ አጣርቶ መስጠት ላይ በጥናት ዳሰሳችን ወቅት ከተነሱ ችግሮች ዋነኛ በመሆኑ፤ የመረጃ አቀማመጥና አሰጣጥ ሂደቱ ግልፅና ወጥነት ያለው በዘመነዋ ቴክኖሎጂ የተገዘ ሊሆን ይገባል። ይህም አላስፈላጊ ክርክርን ለማስቀረተና ለፍትህ አካላትም ፍትሐዊ የሆነ ውሳኔ ለመስጠት ያግዛል። በፍ/ቤት የሚነሱ የመሬት ክርክሮች ረምና የተንዛዛ ሚሆኑበት አንዱ ምክንያት ከመረጃ እጦት በመሆኑ ይሕንን ችግር ለመቅረፍ የመረጃ አሰጣጡ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል። በዚህ ቦታ ላይ የሚሰሩ ባለሞያዎች በተጠያቂነትና በግልፅነት የሚሰሩበትን የአሰራር ሁኔታ መዘረጋት ይኖርበታል።

በጥናቱ በተደረገ ዳሰሳ ለግጭት ምክንያት ከሆኑ ነገሮች አንዱ መሬት የሚሰጥበት መሰፈርት፣ በልማት

ስም የሚነሱ አርሶ አደሮች የካሳ አከፈፈል ሆኔታና ልማት የሚለውን ትረጉም አግባብነት በሌለው መልኩ የአረሶ አደሩን መሬትን ለመውስድ መጠቀምያ ምክንያት መሆኑ ነው፡፡ ይሕም ከመልካም አስተዳደር ችግር ጋር የሚያያዝ በመሆኑ መንግስት ይህን ተከትሎ ችግሩን በጊዜ መቅረፍ የሚስችል አሰራርና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡ የካሳ አከፋፈል ሂደቱን በተመለከተ ጥናቱ በተደረገበት ጊዜ የካሳ ህጉ ያልተሻሻለ በመሆኑ ወቅታዊውን የሀገሪቷን ኢኮኖሚ ያላገናዘበ በመሆኑ አርሶ አደሩን ለከፋ ችግርና የስራ አጥነት ዳርጎል፡፡ ሆኖም ለአርሶ አድሩ የሚከፈል ካሳን በገንዘብ ከማድረግ ይልቅ ምትክ መሬት መስጠት አረሶ አደሩን ከከፋ የስራ አጥነትና በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ያለውን ከገጠር ወደ ከተማ ፍልሰት ለመቀነስ ይረዳል፡፡

ከወል መሬት ጋር በተያየዘ ካለው የመሬት ጥበት ሆነ በተለየዩ ምክንያቶች ይዞታቸውን የማስፋትና በታውን የግል አርጎ የመያዝ ሁኔታ እነዳለ በጥናት ግኝቱ ተመላክቷል ፡፡ በመሆኑም ይህንን ችግር ለመፍታት የውል መሬት በአግባቡ ይዞታውን በመለየት መመዝገቡ ህገወጥ የሆነ የመሬት ወረራን ለማስቀረት እና በዚህ ረገድ የሚነሳን የይገባኛል ክርክርን ለማስቀርት ይጠቅማል፡፡

የገጠር መሬት ጉዳይ ልዳኝ የሚችል እና ለሚነሱ ግጭቶች ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚያስችል እራሱን የቻለ ተቋም መፍጠር ቢቻል

የቤተሰብ አባል የሚለው ሀሳብ በሕግ ለማሕበረሱ ከመስጠት ይልቅ ማሕበረሰቡ እራሱ የቤተሰብ አባሉን ፣በእርሱ ላይ ጥገኛ የሆኑ ግለሰቦችን እንዲወስ ቢደረግ ፡፡በተጨማሪም ጉዳዩ ለውዝግብ ክፍት ከሚሆን የቤተሰብ አባል ምዝገባ መወሰኘ ኩነቶች ምዝገባ በቅድሚያ እዲኖር ቢደረግ ፣ በፍ/ቤት የሚሰጡ ውሳኔዎችም ይህን ምዝገባ መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ ማስቻል

ነገሮች ሁሉ በፍርድቤት ያልቃሉ የሚል የማህበረሰቡ አስተሳሰብ ሊቀየር ይገባል፣ አመራች የግጭት መፍቻ መንገዶችን በመጠቀም ቢቻል የፍ/ቤቶችን ጫና መቀነስ ይቻላል እንዲሁም የማሕበረሰቡን ሀብት እና ጊዜ ይቆጥባል፡፡ለዚህም መንግስት በእያንዳንዱ ቦታ ላይ ጠንከር ያሉ አመራች የግጭት መፍቻ ተቋማት

ቢመሰርት ነገሮች በቀላሉ ያልቃሉ፡፡

በእርሻ መሬት ጉዳይ የሚቀርቡ ማስረጃዎች፤የሰነድም ይሁን የሰው ምስክር አጥጋቢ ባለመሆኑ፡፡ በመሬት ጉዳይ የሚወስኑ የወረዳ ዳኞች በቦታው ሄደው ሁኔታው ማየት ሚችሉ እና የሚወስኑ አሰራር በአሰገዳጅነት ማስቀመጥ ቢቻል፡፡